# ሀገራዊ የአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄ የልማታችን ማዕከል

ኢዛና ዘመንመንፌስ 03/19/14

ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ አንድ ህብረተሰብ እጅ ለእጅ ተያይዘን የሚያካሂዱት ፀረ ድህነት ትግል፣ ግቡ የተጀመረውን ሀገራዊ የሕዳሴ ጉዞ ዳር ማድረስ ነው ። የሕዳሴ ጉዞው የመጨረሻ ግብ ደግሞ ኢትዮጵያን በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ለውድቀት ከዳረጋት ፈርጀ ብዙ ድህነት ማላቀቅና ወደቀደመው ታላቅነቷ እንድትመለስ ማድረግ እንደሆነ ተደጋግሞ ተነግሯል። ከዚህ አጠቃላይ ሀገራዊ መግባባት ውጭ የሚሆን አንገብጋቢ አጀንዳ በዛሬዋ ፌዴራላዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ነባራዊ እውነታ ውስጥ ቦታ የለውም፡፡

ባለፈው የጋራ ታሪካችን አውቀንም ይሁን ሳናውቅ የፈፀምናቸው መሰረታዊ ስህተቶች ያስከተሉትን ፈርጀ ብዙ ጥፋት ማረምና ከዚህ በኋላ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የማይደገምበትን ፅኑ መሰረት የመጣል ታሪካዊ ሃላፊነትን የተሸከመ ኢትዮጵያዊ ትውልድ አካል ነን። የሚል አሁን አገራችን የምትገኝበት የሕዳሴ ጉዞ ከቀን ወደ ቀን ስፋትና ጥልቀቱ እየየጨመረ የሚሄድበትን የተቀናጀ ጥረት ይበልጥ አጠናክሮ ማስቀጠል ፈፅሞ ችል መባል የሌለበት የህልውና ጉዳይ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን በሌላው ዓለም ህብረተሰብ ዘንድ የምንታወቅባቸውን የህብረ ብሔራዊ ማንነታችን መገለጫዎች ወይም ብዝሃነታችንን በቅጡ ለማስተናገድ የሚያስችል አንድ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር ባለመ የጋራ መግባባት ላይ ተመስርተን የተያያዝነውን ፈርጀ ብዙ የህዳሴ ጉዞ ለማሳካት ሲባል የሚደረግ እርብርብ የማይመለከከተው ዜጋ ሊኖር አችልም።

እንግዲያውስ በዚሁ አዲሲቷን ፌደራላዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ወደ ቀደመው የገናናነት ታሪኳ ለመመለስና ከትላንቱ የጨለማ ዘመን የወረስነውን አሳፋሪ አገራዊ ገፅታችንን ሙሉ ለሙሉ ቀይረን በዓለም ህዝብ ፊት የጋራ ማንነታችን መገለጫ

ተደርጎ እስከመቆጠር ደርሶ የቆየው ፈርጀ ብዙ ድህነት ተረት  ሆኖ የሚቀርበትን ክቡር ተልዕኮ ለማሳካት ባለመ የቁርጠኝነት መንፈስ ክንዳችንን አሰተባብረን ለምናካሂደው መጠነ ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ የአካባቢ እንክብካቤንም ማጠቃለል ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ ባለፉ አምስት ዓመታት ታላቅ አገራዊ ንቅናቄ ተፈጥሮ በተፋሰስ ልማት የአካባቢ እንክብካቤ ሰራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በእርግጥም ደግሞ ይህችን ኢትዮጵያ የምንላትን የጋራ ቤታችንን አንድ ወቅት ከገጠማት አሳዛኝ ውድቀት አንስተን ወደ ቀደመው የታላቅነት ታሪኳ እንድትመለስ ማድረግ ካለብን በደን መራቆት ምክንያት እርቃናቸውን ቆመው የቀሩ ኮረብታዎችና ሸንተረሮቿን እንዲሁም የደን መራቆቱ ድምር ውጤት በሆነው ተደጋጋሚ የዝናብ እጥረት (ድርቅ) እየተመቱ ወደ በረሃማነት የተለወጡ ሜዳና ሸለቆዎቿን ዳግም እንዲያገግሙ ማድረግ የጥረታችን ሁሉ ቁልፍ ተግባር መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ስለዚህም አንድ ወቅት ላይ፣

"እምዬ ኢትዮጵያ፣ ለምለሚቱ አገሬ
በጣም ደስ ይለኛል፣ ከአንቺ መፈጠሬ…!"

እያሉ አበው ከያኒያን እንዲያዜሙላት ያስገደዳቸውን አረንጓዴ ውበት የተጎናፀፈች እናት ሀገር ትኖረን ዘንድ፣ ከፈርጀ ብዙው ድህነታችን ጋር የምናካሒደው የሞት ሽረት ትግልና የፀረ ድህነት ትግሉን በድል አድራጊነት ለመወጣት ሲባል ኢትዮጵያውያን  እንደ አንድ ህብረተሰብ እጅ ለእጅ ተያይዘን የምናደርገው የልማት እርብርብ ሁሉ የአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄን ባማከለ ዘለቄታዊ ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሀገር አቀፋዊ መርሐ-ግብር መንደፍ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ጉዳይ ነው ፡፡

በዚህ ረገድ እስከዛሬ የተስተዋለውን አገር አቀፍ እንቅስቃሴ እንገምግም  ከተባለ ደግሞ በተለይም የትግራይ፣ የአማራና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች እንደየቅደም ተከተላቸው ያደረጉት አርአያነት ያለው ጥረትና ያስመዘገቡት አበረታች ውጤት ተጠቃሽ ነው፡፡ የሶስቱ ክልላዊ  መንግስታት ቀደም ካሉት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዓመታት ጀምሮ የአካባቢ ጥበቃን ዕቅድ ነድፈው ለተግባራዊነቱ የየበኩላቸውን አበረታች ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወሳል፡፡ በተለይም ደግሞ ትግራይ በምስራቃዊ ዞን አፅቢ.ወንበርታ ወረዳ

ውስጥ የሚገኙ ታታሪ አርሶ አደሮች በዘርፉ ያሳዩት እንቅስቃሴና ያስመዘገቡት አመርቂ ውጤት ክልሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ የአርአያነትን "ሪከርድ" ይዞ እንዲቆይ አድርጎታል።

አሁን-አሁን በሌሎቹ ክልላዊ መስተዳድሮች የሚኖረው ህበረተሰባችንም የእርከን ስራ ለአካባቢ ጥበቃ ያለውን ተጨባጭ ጠቀሜታ በመረዳት ረገድ መሰረታዊ ሊባል የሚችል የአመለካከት ለውጥ እያመጣ ነው። በዚያው ልክ ስፋትና ጥልቀቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ሀገር አቀፉዊ የህዝብ ንቅናቄ መፍጠር ችሏል።

ከዚህ አኳያ መላው ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለሚያካሂዱት ሀገራዊ የፀረ ድህነት ትግል እንደ ማዕከል በሚቆጠር መልኩ እጅግ በጣም እየተጋጋለ ሲቀጥል የሚስተዋለውን የአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄ መመልከት ነባራዊውን እውነታ በቅጡ እንረዳ ዘንድ ያስችለናል። የአካባቢ ጥበቃ ማህበረሰባዊ ንቅናቄን ሀገር አቀፍ ገፅታ የማላበስ ጥረት በማድረግ ረገድ የአማራና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልሎች በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቀዳሚ ስፍራ እየያዙ መጥተዋል። ከአማራው ክልል የአካባቢ ጥበቃውን ህዝባዊ ንቅናቄ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ በመጣ ስፋትና ጥልቀት አጧጡፈው እንደቀጠሉበት ከሚነገርላቸው የምስራቅ ጎጃምና የደቡብ ወሎ ዞኖች ቀዳሚዎቹ ተጠቃሾች ናቸው። ከኦሮሚያም አርሲ ዞን በአርአያነት የሚጠቀስ ውጤት እንዳስመዘገበ ይታወቃል።

ይህ ሊሆን የቻለው የህዝብ ብዛታቸው የአንደኛና የሁለተኛነት ደረጃን የሚይዙ ክልላዊ መስተዳድሮቻችን፣ ቀደም ሲል የትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግስት በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ካካሄደው የፈር ቀዳጅነት ተግባራዊ እንቅስቃሴና እንቅስቃሴው ካስገኘው አመርቂ ውጤት የቀሰሙትን ጠቃሚ ልምድ መሰረት ባደረገ መልኩ የየራሳቸውን አርሶ አደር ህብረተሰብ ስለጉዳዩ አስፈላጊነት የማሳመን ስራ ከመሰራታቸው የተነሳ ነው። የእያካባቢው ህዝብ በደን መራቆት ምክንያት የሚከሰቱ ፈርጀ ብዙ አደጋዎች እየተበራከቱ በመጡ ቁጥር ለተደራራቢ ማህበራዊ ቀውስ መዳረጉ እንደማይቀር በሚገባው ቋንቋ ሲነገረውና እውነታውን በቅጡ መገንዘብ ሲችል እንደ ህብረተሰብ ህልውናውን ከጋራ ጥፋት የሚታደግ ዘላቂ መፍትሄ ለመሻት እንብዛም እንደማይቸገር ደግሞ አሁን ሀገር አቀፉዊ ይዘት እየተላበሰ ሲሄድ ከሚስተዋለው የኢትዮጵያውያን ብሄር ብሄረሰቦች የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ዘመቻ ወይም የአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄ መረዳት አያዳግትም።

በአጠቃላይ አካባቢን መጠበቅ የህልውና ጉዳይ እንደሆነ የጋራ ግንዛቤ በተያዘባቸው ክልሎቻችንን ቀደም ካሉት ዓመታት ጀምሮ ሲከናወን የቆየው የህዝብ ንቅናቄን መሰረት ያደረገ የደን ልማት ተግባር ድምር ውጤቱ ሲመዘን በዚህ ረገድ እንደሀገር የተደረጉ ጥረቶች ከሞላ ጎደል ፍሬያማ ለመሆን በቅተዋል።

ለምሳሌ  ከአማራ ብሄራዊ ክልል የደቡብና ሰሜን ወሎ ዞኖች እንዲሁም ከኦሮሚያ ምስራቅ ሸዋና በተለይ ደግሞ አርሲ ዞን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ቀደም ሲል ሙሉ ለሙሉ ነጥፈው የነበሩ በርካታ ምንጮች እንደገና እየፈነዱ ለመስኖ እርሻ አገልግሎት የሚውል የውሃ ፍጆታ እስከመስጠት እንደደረሱ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ማለትም ከዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ይፋ መሆን በፊት በነበሩት ዓመታት የትግራይ ክልል ብቻ እንደ አርአያ ሲጠቀስ እንሰማው የነበረውን የአካባቢ ጥበቃ ስኬት ዛሬ ሀገር አቀፋዊ ገፅታ እያላበስነው ስለመሆናችን የሚያረጋግጥልን ነባራዊ ሀቅ ነው ማለት ይቻላል።

እርግጥ የእስከዛሬው የአካባቢ ጥበቃ ጥረት ያስገኘውን ውጤትና አሁን  ያለበት ወቅታዊ ገፅታ ምን እንደሚመስል እንገምግመው ከተባለ፣ እውነታው ምናልባትም “ዓባይን በጭልፋ” ከመሆን ላያልፍ ይችል ይሆናል። ምክንያቱም አንደኢትዮጵያ እጅግ ስር የሰደደ ድህነትና ኋላቀርነት ተንሰራፍቶበት በቆዩ ሀገር ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ህብረተሰብ የደን ሀብትን ጠቀሜታ በውል ተገንዝቦ ተፈጥሯዊ አካባቢውን  ከቀውስ ለመከላከል ተግባር ትኩረት አይሰጥምና። እናም ባለፈው የውድቀት ታሪካችን የፈፀምነው ስህተት መጠነ ሰፊ ጉዳት ከማስከተሉ የተነሳ ጥሎት ያለፈው ጠባሳም እንዲህ በቀላሉ የሚሽር አይደለም።

ስለዚህ  ኢትዮጵያውያን  አንድ ወቅት በድህነትና በሁዋላቀርነት ምክንያት ለከፋ የደን መራቆት አደጋ የዳረግናትን  ሀገራችንን ይሄው አካባቢያዊ ቀውስ ተባብሶ ቢቀጥል ሊያደርስ ከሚችለው አጠቃላይ ጥፋት ለመታደግና ወደቀድሞው አረንጓዴ ይዞታዋ ተመልሳ ለማየት እንችል ዘንድ፣ የአካባቢ ጥበቃ ሀገራዊ ንቅናቄያችን ሁሉንም የክልል መስተዳድሮች በሚሸፍን ስርጭት ይበልጥ ተጠናክሮ መካሄድ ይኖርበታል።

እያንዳንዱ ክልላዊ መንግስት ለሚያስተዳድረው የብሔር ብሔረሰብ ህዝብ አካባቢ ጥበቃ የሀገራዊ ህዳሴያችን መገለጫ ከሆኑት ቁልፍ ተግባራት መካከል እንደሚመደብ የተሟላ ግንዛቤ ማስጨበጥ ከቻለና አሁን በዚህ ረገድ ከቀን ወደቀን እየተጋጋለ ሲሄድ

የሚስተዋለው የትግራይ፣ የአማራና የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልሎች አበረታች የደን ልማት ንቅናቄ ተደራሽነቱን እያሰፋ እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚጠበቅብን እንደህብረተሰብ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ከቻልን፣ ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር አረንጓዴ ሆና የምናይበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን  መናገር ይቻላል።

መቸስ ለሀገር ለወገኑ በጎ በጎውን የሚመኝ ቅን አሳቢ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ  ሌላው ቢቀር፣ ከየክልሉ ህዝብ ጋር በአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄው የመሳተፍና መጭውን ትውልድ ከበረሃማነት በመታደግ ረገድ ባለውለታ የሚያደርገውን አሻራ ለማኖር የሚያስችለውን መልካም ዕድል መጠቀም አለበት።

በአንድ አገር ዜጎች መካከል የፖለቲካዊ አቋም ወይም የርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት ልዩነት ቢኖር እንኳን የአካባቢ ጥበቃ ንቅናቄን በመሳሰሉ ለጋራ ዕጣ - ፈንታቸው ዘላቂ ዋስትና በማስቀመጥ ረገድ ወሳኝ አስተዋፅኦ በሚያበረክቱ የልማት አጀንዳዎች ላይ አብረው እንዳይሰለፉ ሊያግዳቸው አይገባም።

አለበለዚያ ግን እንዲህ ዓይነቱን እጅግ በጣም ወርቃማ ሊባል የሚችል ታሪካዊ አጋጣሚ ተጠቅመው ለሀገራቸው ዳግም ልደት እውን መሆን አንዳች በጎ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበትን የአካባቢ ጥበቃ ህዝባዊ ንቅናቄ ለመቀላቀልና መጭውን ትወልድ በረሃማነት ከሚያስከትለው ስነ የተፈጥሮ አካባቢ  ቀውስ ለመታደግ ያለመቻልን ያስከትላል። ይህ ደግሞ “ለአገር አስባለሁ፤ ራዕይ አለኝ” ከሚል ፖለቲከኛ የሚጠበቅ አይደለም።

ስለዚህ የህዳሴው ዘመን ኢትዮጵያዊነት የሚጠይቀውን የተግባር ሰውነት ለማሟላት ከምንም ነገር በላይ “አስፈላጊው ጉዳይ ይህ ወርቃማ የታሪክ አጋጣሚ በዋዛ ፈዛዛ ሊያመልጠኝ አይገባም” ከሚል የልብ ቅንነት በመነጨ ሀገራዊ የህዳሴ መንፈስ ራስን ለመልካም ተግባር ማዘጋጀትና የታሪካዊ ሒደቱ አካል ሆኖ መገኘትን በፍፁም የበጎነት ስሜት አምኖ መቀበል አሰፈላጊ ነው። ይህን አዲስ አስተሳሰብ ለመላበስ  የሚያስችል ልባዊ ፍቃደኝነትን ያሳየ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ዜጋ ሁሉ መላው የሀገራችን ህዝቦች በፈርጀ ብዙ ድህነትና ኋላቀርነት ላይ የሚያካሒዱትን የሞት ሽረት ትግል ዳር ቆሞ የሚመለከትበት ምክንያት አይኖረውም።